**አገልግሎቶች (የሚሰጡመረጃዎች)፡ -**

በባህር ዳር ከተማ ስር ለሚገኙ ከቀበሌ እስከ ክልል ቢሮ እንዲሁም ለአንዳንድ የልማት ተቋማት የመንግስት ሠራተኞች ጥዋትና ማታ የሰርቪስ አገልግሎት መስጠት ፤ ከባህር ዳር ከተማ ውስጥ ለሚገኙ ለሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች በዝቅተኛ ታሪፍ ሳምንቱን ሙሉ ከ12፡ 00 እስከ ምሽት 4፡ 00 ሠዓት የትራንስፖርት አገልግሎት ህዝብ ከሚበዛባቸው ቦታዎች በመገኘት ሰርቪስ አገልግሎት መስጠት፡ ፡

ባለን ዘመናዊ ጋራዥ ለመንግስት ተቋማት ተሸከርካሪዎች ጠቅላላ ጥገና አገልግሎት መስጠትና እንዲሁም በተጨማሪ ለግል መኪና ባለቤቶች ደግሞ የእጥበትና ለኤሌክትሪክ ተሸከርካሪዎች ደግሞ የቻርጀር አገልግሎት መስጠት፡ ፡

ለሀዘንና ለተለያዩ አገልግሎት ለሚፈልጉ ግለሰቦችና ተቋማት የኩንትራት የትራንስፖርት አገልግሎት በተመጣጣኝ ዋጋ መስጠት፡ ፡

**<u>ስልጣንና ተግባር፡ -</u>**

ሀ/ ኢንተርፕራይዙ ለፐብሊክ ሰርቪስ ሰራተኞች (ከጠዋቱ 2፡ 15 ስራ ቦታ አካባቢ ማድረስ 11፡ 30 በኋላ ከስራ ቦታ ወደ መኖሪያ አካባቢ ማድረስ) በአሰሪ መ/ቤቶች ክፍያ ነፃ አገልግሎት መስጠት፡ ፡

ለ/ከመንግስት የስራ መግቢያና መዉጫ ሰዓት ዉጭ እንዲሁም በበዓላት ቀናትና ለተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ተመጣጣኝ የትራንስፖርት ታሪፍ በማስቀመጥ ገቢ መሰብሰብ፣ተጨማሪ ገቢ ለማግኘት የገበያ ጥናት በማድረግ ገቢዉን ማሳደግ በገቢዉ መተዳደር፣

ሐ/አገልግሎቱ ለመንግስታዊና መንግስታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች ለኩባንያዎች ፣ለትምህርት ቤቶች፣ ለማህበራትና የህዝብ አደረጃጀቶች ለረዥም ጊዜ የአገልግሎት ጉዞዉን መስመር ርቀት በመለካት የኮንትራት ዉለታ በመፈራረም አገልግሎት መስጠት፣

መ/አገልግሎቱ መንግስታዊ ለሆኑና ላልሆኑ ድርጅቶች ፣ለማህበራት፣ ለአደረጃጀቶች፣ ለክበባትና ለግለሰቦች ለነጠላ ወይም ለደርሶ መልስ ጉዞ አገልግሎት መስጠት፣

ሠ/የጥገና ወርክ ሾፑን መሳሪያዎችና ማሽኖች በማደራጀት ለድርጅቱ አነስተኛና ከፍተኛ ተሽከርካሪዎች አጠቃላይ ጥገናና ዕድሳት አገልግሎት መስጠት፣ የተሽከርካሪ አካል ዕድሳት ፣የቀለም ቅብና ታፒሰሪ ስራዎች መስራት ፣ የተሽከርካሪ ዩኒቶችን በሞዲፊኬሽንና በማንፋክቸሪንግ የማምረትና የመጠገን ስራዎች፣

ረ/ከድርጅቱ ዉጭ የሚቀርቡ የተሸከርካሪ ጥገና ጥያቄዎችን በመቀበልና ዉል በመፈራረም አዋጭ በሆነ ዋጋ ጠግኖ ለባለ ንብረቱ ማስረከብን ያካትታል፡፡

ሰ/ የተሽከርካሪ የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ ጥያቄ መቀበል፣ የብቃት ማረጋገጫ ክፍያ ማስከፈል፣ ተሽከርካሪዉን በማሽን መመርመር፣ ተሽከርካሪዉንና የምርመራ ዉጤቱን ለሹፌሩ ወይም ለባለንብረቱ ማስረከብ፣